የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.50
ADDIS ABABA 20th July, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፪/፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሳዑዲ አረቢያ ንጉሳዊ መንግሥት መካከል የተደረገ የቤት ሰራተኞች ቅጥር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………….……...…ገጽ ፲ሺ፬፻፬

## Content

Proclamation No. 1092/2018

The Agreement on the Employment of Domestic Workers between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Kingdom of Saudi Arabia Ratification Proclamation.--……………..Page 10404

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፪/፪ሺ፲

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሳዑዲ አረቢያ ንጉሳዊ መንግሥት መካከል የተደረገውን የቤት ሰራተኞች ቅጥር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሳዑዲ አረቢያ ንጉሳዊ መንግሥት መካከል የቤት ሠራተኞች ቅጥር ስምምነት ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በጅዳ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1092/2018

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE EMPLOYMENT OF DOMESTIC WORKERS BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE KINGDOM OF SAUDI ARABIA**

WHEREAS, The Agreement on the Employment of Domestic Workers between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the kingdom of Saudi Arabia has been signed on the 25th day of May, 2017 in Jeddah.

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 28th day of June, 2018.

NOW, THEREFORE, in accordance with the Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሳዑዲ አረቢያ ንጉሳዊ መንግሥት መካከል የተደረገ የቤት ሰራተኞች ቅጥር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፪/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሳዑዲ አረቢያ ንጉሳዊ መንግሥት መካከል ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በጅዳ የተፈረመው የቤት ሰራተኞች ቅጥር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>**

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የፌደራልና ክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይህን ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "The Agreement on the Employment of Domestic Workers between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Kingdom of Saudi Arabia Ratification Proclamation No. 1092/2018".

**2. <u>Ratification of Agreement</u>**

The Agreement of the Employment of Domestic Workers between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Kingdom of Saudi Arabia, signed on the 25th day of May, 2017, is hereby ratified.

**3. <u>Implementing organ</u>**

The Ministry of Labor and Social Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to undertake all acts necessary to the implementation of this Agreement in cooperation with concerned federal and regional government organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the *Federal Negarit Gazettee*.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of July, 2018.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me